# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት

## ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ

## SOUTHWEST NEGARIT GAZETA

## OF THE SOUTHWEST ETHIOPIA PEOPLES REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| ……. ዓመት ቁጥር……<br>…….. ቀን……./2014 | ………th Year No ………<br>………..th ……., 2021 |


---

## ማውጫ

### አዋጅ ቁጥር 2/2014 ዓ.ም


የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት “ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ”ን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 2/2014 ……………….. ገጽ ፩


---

## አዋጅ ቁጥር 2/2014

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት “ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ”ን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

### መግቢያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ ለክልሎች በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፤ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ህገ መንግስት አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) ለክልሉ ም/ቤት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 2/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. መቋቋም

1. በዚህ አዋጅ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት “ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ” እየተባለ የሚጠራ የክልሉ መንግስት ጋዜጣ ተቋቁሟል፡፡
2. በዚህ ጋዜጣ ማናቸውም አዋጅ፣ ድንጋጌ፣ ህግ፣ ደንብ፣ ማስታወቂያና ከዚህም የተዋጣ ደንብና መመሪያ ሁሉ፣ እየታተመ ይወጣል፡፡

3. ጋዜጣውን የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ምክር ቤት ይህን የክልሉን ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ ስራውን ያደራጃል፤ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች እየታተመ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

4. የጋዜጣው ስያሜ

ይህ የክልሉ መንግስት ጋዜጣ በማናቸውም በህግ ረገድ በሚጠቅስ ነገር ሁሉ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ እየተባለ ይጠቀሳል፡፡

5. የመቀበል ግዴታ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት "ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ" ታትሞ ሲወጣ በማናቸውም ፍርድ ቤት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ ድርጅት እና ግለሰብ፤ ማናቸውንም አዋጅ፣ ድንጋጌ፣ ህግ፣ ደንብ፣ ውሳኔ፣ ትዕዛዝ፣ ማስታወቂያ ከእነዚህም የተዋጣ ደንብና መመሪያ ሁሉ መቀበል አለበት፡፡

6. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቦንጋ

ህዳር 15/ 2014 ዓ.ም

ዶ/ር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት

ርዕሰ መስተዳደር